Washington State Health Care Authority

Washington State Department of Social & Health Services — Transforming lives

# የጤና ክብካቤ ሽፋን መብቶች እና ግዴታዎች

**Health Care Coverage Rights and Responsibilities**

## የእርስዎ መብቶች (እኛ የሚከተለውን ማድረግ አለብን)

**ለሁሉም የጤና ክብካቤ ሽፋን ፕሮግራም**

**እርስዎ የተጠየቁትን ቅጾች እንዲያነቡ እና እንዲሞሉ ልናግዝዎት ይገባል።** እገዛ ከፈለጉ የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች መምሪያን (DSHS) በ 1-877-501-2233 ማነጋገር ይችላሉ፡፡

ከ DSHS ወይም የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን (HCA) ጋር በሚነጋገሩበት ወቅት **የአስተርጓሚ ወይም የትርጉም አገልግሎት** በነጻ ሳንዘገይ እናቀርብልዎታለን፡፡

**የእርስዎን የግል መረጃዎች በሚስጢር እንይዛለን** ነገር ግን እኛ የተወሰኑ መረጃዎችን ከሌሎች ፋይናንሳዊ ድርጅቶችና HCA ኮንትራክተርና ድጋፍ እና ከፌዴራል ተቋማት ጋር ለፕሮግራሙ ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ እና ለምዝገባ ልናጋራ እንችላለን።

በDSHS ወይም HCA በተሰጠው ውሳኔ ላይ በተላለፈው ለጤና ሽፋን፣ የረዥም ጊዜ አገልግሎቶች እና ድጋፎች (LTSS) ወይም ለጤና እቅድ ብቁ ለመሆን ተጽእኖ በሚያሳድር ውሳኔ ካልተስማሙ **ይግባኝ የማቅረብ እድል ይሰጥዎታል፡፡** ይግባኝ ከጠየቁ ጉዳይዎት በድጋሚ ይታያል፡፡ ለ DSHS መርሀግብሮች ይግባኝ ስለመጠየቅ መረጃ ለማግኘት የ DSHS የባለጉዳይ አገልግሎት መገኛ ማዕከልን በ1-877-501-2233 ያነጋሩ ወይም የአካባቢዎት የማህበረሰብ አገልግሎት ጽ/ቤትን ይጎብኙ፡፡

ይግባኙ በገምጋሚ ኮሚቴ ያልታየ የ Washington Apple Health ሽፋንን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበ ከሆነ እርስዎ ጉዳይዎ የሚሰማበት የአስተዳደራዊ ችሎት ቀጠሮ ይያዝልዎታል።

**ብፍትሐዊ መንገድ ልንይዝዎ ይገባናል። መድልዎ እና ልዩነትን ማንጸባረቅ ሕገወጥ ድርጊት ነው።** DSHS እና HCA ተገቢውን የፌደራል የሰብአዊ መብቶች ህጎችን ያከብራሉ እንዲሁም በዘር፣ ቀለም፣ ብሄር፣ እድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ ወይም ጾታ መሰረት መድልኦ አያደርጉም፡፡ DSHS እና HCA በዘር፣ ቀለም፣ ብሄር፣ እድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ ወይም ጾታ ምክንያት ሰዎችን አያገሉም ወይም በተለየ መልኩ አያስተናግዱም፡፡

እንዲሁም DSHS እና HCA ተገቢውን የግዛት ህጎች ያከብራሉ፣ በእምነት፣ ጾታ፣ ጾታዊ ማንነት ወይም አስተያየቶች፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ የትዳር ሁኔታ፣ ሀይማኖት፣ በክብር የተሰናበተ ወራድር በመሆን ወይም በወታደራዊ ሁኔታ ወይም የአካል ጉዳተኛ ሰው በሰለጠነ ውሻ መመራት ወይም በእንስሳ መገልገል ሁኔ መሰረት መድልኦ አያደርጉም፡፡

DSHS እና HCA፡

- አካል ጉዳተኛ ሰዎች ከእኛ ጋር በተሻለ መግባባት እንዲችሉ የሚከተሉትን ነጻ ድጋፎች እና አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡
    - ብቃት ያለው የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ
    - በሌላ መንገድ የሚዘጋጅ በጽሑፍ የሚቀርብ መረጃ (በትልልቅ ፊደላት፥ በድምፅ፥ በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የኤለክትሮኒክ ፎርማቶች፥ ሌሎች ፎርማቶች)
- የሚከተሉትን ነጻ የቋንቋ አገልግሎቶች የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ላልሆኑ ሰዎች ይሰጣሉ
    - ብቃት ያላቸው ተርጓሚዎች
    - በሌላ ቋንቋዎች የተዘጋጁ በጽሑፍ የሰፈሩ መረጃዎች

እነዚህን አገልግሎቶች ከፈለጉ በ1-877-501-2233 ይደውሉ፡፡

DSHS ወይም HCA እነዚህን አገልግሎቶች አላቀረቡም ወይም በሌላ መልኩ መድልኦ አድርገዋል ብለው ካመኑ ለሚከተለው ቅሬታ ማሰማት ይችላሉ፡

- **DSHS**
  ATTN: Constituent Services
  PO Box 45131
  Olympia, WA 98504-5131
  1-800-737-0617
  Fax: 1-888-338-7410
  **askdshs@dshs.wa.gov**
- **HCA Division of Legal Services**
  ATTN: Compliance Officer
  PO Box 42704
  Olympia, WA 98504-2704
  1-855-682-0787
  Fax: 1-360-586-9551
  **compliance@hca.wa.gov**

በግንባር ቀርበው ወይም በስልክ፣ በፖስታ፣ ፋክስ ወይም በኢሜል ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ቅሬታ ለማሰማት እርዳታ ከፈለጉ የ DSHS መሰረታዊ አገልግሎቶች ወይም የ HCA የህግ አገልግሎቶች መምሪያ ሊረዳዎት ዝግጁ ነው፡፡

በተጨማሪ የሲቪል መብቶች ጥሰት አቤቱታን ወደ the U.S. Department of Health and Human Services, Office for Civil Rights በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በ **https://ocrportal.hhs.gov/ocr/portal/lobby.jsf** ላይ ወይም በሚከተሉት አድራሻዎች በደብዳቤ ወይም በስልክ ማቅረብ ይችላሉ፡-



HCA 18-011 AM (12/18) Amharic

**U.S. Department of Health and Human Services**
200 Independence Avenue, SW
Room 509F, HHH Building
Washington, D.C. 20201

1-800-368-1019, 800-537-7697 (TDD)።

የአቤቱታ ቅጾችን በሚከተለው አድራሻ ላይ ሊያገኙት ይችላሉ፦ www.hhs.gov/ocr/office/file/index.html.

# የእርስዎ ግዴታዎች (የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት)

## ለሁሉም የጤና ክብካቤ ሽፋን ፕሮግራም

**የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር እና የኢሚግሬሽን ሁኔታ መረጃ።** ከተወሰኑ ማግለያዎች ጋር እርስዎ የራስዎን ወይም ለጤና ክብካቤ ሽፋን ማመልከት የሚፈልግ ማንኛውም በቤትዎ ውስጥ የሚገኝ ግለሰብ ማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የስደተኛ ሰነድ ቁጥር መስጠት አለብዎት። የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር ለጤና ኢንሹራንስ የአረቦን ግብር የዱቤ ክፍያ አገልግሎት ለማግኘት ለማመልከት አስፈላጊ ነው። እኛ ይህንን መረጃ የእርስዎን ማንነት፣ ዜግነት፣ የኢሚግሬሽን ሁኔታ፣ የትውልድ ቀን እና የሌላ ጤና ክብካቤ ሽፋን መኖር አለመኖር በማረጋገጥ እርስዎ ለፕሮግራሙ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን እንጠቀማለን። እኛ ይህንን መረጃ ለማንኛውም የኢሚግሬሽን ኤጀንሲ አናጋራም።

እርስዎ ለቤተሰብዎ አባል ለሆነ ግለሰብ ማመልከት ይችላሉ፤ ነገር ግን ለሌሎች ግለሰቦች ማመልከት አይችሉም። ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የስደተኛ ሰነድ ቁጥር ከሌልዎት ሌሎች ለእነሱ አመልክተው ሽፋኑን ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ምንም እንኳን ለመድን ሽፋን እርስዎ ብቁ ባይሆኑም ለእርስዎ ልጅ ግን ማመልከት ይችላሉ። ማመልከቻ ማቅረብ የእርስዎን የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ቋሚ ኗሪ ወይም ዜጋ ለመሆን ያልዎት ዕድሎች ላይ ተጽዕኖ አይኖራቸውም።

በሀገሪቱ ውስጥ በሕጋዊ መንገድ እየኖሩ የሚገኙ መሆናቸውን ማሳየት ለማይችሉ ሰዎች የሚሰጥ የተወሰኑ የ Washington Apple Health ፕሮግራሞች አሉ። ነገር ግን እርስዎ የቤተሰብዎ አባል ለሆነ ግለሰብ የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SSN) ወይም የስደተኛ ሰነድ ቁጥር ለማቅረብ ካልፈለጉ ያላመለከተ ግለሰብ ገቢ በተመለከተ መረጃውን ለማግኘት በእርስዎ ላይ ክትትል ማድረግ ይጠበቅብናል።
**በኤጀንሲው ከተጠየቀ** እርስዎ ለፕሮግራሙ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን የሚያስፈልግ ማንኛውንም መረጃ ወይም ማስረጃ ያቅርቡ።

# እርስዎ ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

## ለሁሉም የጤና ክብካቤ ሽፋን ፕሮግራም

የ Washington Connection እና በክልል የሚተዳደሩ የማመልከቻ ስርአቶች አሰራርን፣ እነዚህን ሲጠቀሙ ያለዎት መብት እና ግዴታን እና ከእነዚህ የሚያገኙትን ሽፋን የሚያስተዳድሩ **የተወሰኑ የግዛት እና የፌደራል ህጎች አሉ፡፡** እነዚህን ሥርዓቶች በመጠቀምዎ በተጠቃሚዎች እና በሽፋኑ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑትን ሕጎች ለማክበር ተስማምተዋል።

**በ1973 እ.ኤ.አ የወጣው ብሔራዊ የመራጭ ምዝገባ ደንብ** ሁሉም ግዛቶች በሕዝብ ድጋፍ ሰጪ ጽ/ቤቶቻቸው አማካይነት የመራጭ ምዝገባ እገዛ እንዲሰጡ ያስገድዳቸዋል። የእርስዎ ምርጫ ለመምረጥ መመዝገብ ወይም አለመመዝገብ በዚህ ኤጀንሲ በሚሰጥዎት አገልግሎቶች ወይም ጥቅማጥቅሞች ላይ ምንም ዓይነት ተጽእኖ አያሳድርም። እርሰዎ ምርጫ ለመምረጥ በድህረ ገጽ **www.vote.wa.gov** ላይ በመግባት ወይም የመራጭ ምዝገባ ቅጽ በስልክ ቁጥር 1-800-448-4881 ደውለው በማዘዝ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

የእርስዎን ወይም የቤተሰብዎትን አባል የጤና መረጃ በተመለከተ HCA እና DSHS ከሌላ ሰው ጋር፣ ፈቃድ ያለው ተወካይን ጨምሮ ህጋዊ ውክልና ከሌለው ወይም መረጃው እንዲሰጥ እርስዎ የስምምነት ቅጽ ካልፈረሙ በስተቀር እንዳይወያዩ **የጤና መድህን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ** (HIPAA) ገደቦች ይከለክላል፡፡ ይህ መረጃ የአእምሮ ጤናዎ፥ የኤች.አይ.ቪ.፥ የኤድስ፥ የአባላዘር በሽታን ውጤት፥ ወይም ስለሚያገኙት ሕክምናና መድሃኒት የሚገልፅ መረጃ የሚያካትት ነው።

የእርስዎን ወይም የቤተሰብዎትን አባል በግል የሚለይ መረጃን (PII) HCA እና DSHS ለመረጃውን ለመቀበል ፈቅድ ለሌለው ሌላ ሰው እንዲሁም ያለእርስዎ ፈቃድ እንዳይሰጡ **ተስማሚ ዋጋ ያለው የእንክብካቤ ህግ** ይከለክላል፡፡

**ለ DSHS እና HCA የሚሰጡት መረጃ** ለጤና እንክብካቤ ሽፋን ብቁነትዎን ለመወሰን እንዲያስችል በፌደራል እና የክልል ሰራተኞች ይረጋገጣል፡፡ ማረጋገጫው በኤጀንሲው ሠራተኞች የሚደረግ ክትትል ጉብኝቶችን ሊያካትት ይችላል።

**HCA እና DSHS የጤና መድህን እቅድዎትን የማስተዳደር ሀላፊነት የለባቸውም፡፡** የእርስዎ የጤና ኢንሹራንስ አቅራቢ ስለ ጥቅማጥቅሞችዎ የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል። **ስለጤና መድህንዎት እቅድ ህጎች፣ ሊያገኙ ስለሚችሉት ጥቅሞች እና የጥቅም ጥያቄ ስለማቅረብ ወይም ጥቅም ሲከለከል ይግባኝ ስለማቅረብ ጥያቄ ካለዎት የጤና መድህን አቅራቢዎትን ያነጋግሩ፡፡**

***እርስዎ በህፃናት ድጋፍ ዋና ክፍል (Division of Child Support (DCS)) አማካይነት የድጋፍ ማስፈፀሚያ አገልግሎት ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።***
የእነዚህ አገልግሎቶች ማመልከቻ ለማግኘት **www.childsupportonline.wa.gov** ይጐብኙ ወይም በእርስዎ አካባቢ የሚገኙ የህፃናት ድጋፍ ዋና ክፍል ጽ/ቤት ያነጋግሩ

# የእርስዎ መብቶች (እኛ የሚከተለውን ማድረግ አለብን)

## ለ Washington Apple Health ብቻ

***ስለ መብትዎና ግዴታዎ መናገር ይኖርብናል***
*ጥያቄውን ካነሱብን።*

ቢያንስ የእርስዎን ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ ወይም የአመልካቹ ሕጋዊ ወኪል ፊርማ ያካተተ **ከፊል ማመልከቻ እንዲያቀርቡ እንፈቅዳለን።** እኛ የከፊል ማመልከቻውን የተቀበልንበት ቀን የእርስዎ ሽፋን ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ሲሆን ይህ የእርስዎ የማመልከቻ ቀን ነው። እርስዎ ማመልከቻዎን እስከሚያሟሉ ድረስ ለእርስዎ ስለሚሰጥ ሽፋን እኛ የመጨረሻ ውሳኔ አናስተላልፍም

በ WAC 182-503-0005 ሥር የተዘረዘረውን ማንኛውም ዘዴ በመጠቀም **ማመልከቻ ወይም ከፊል ማመልከቻ እንዲያቀርቡ እንፈቅድልዎታለን።**

**የእርስዎን ማመልከቻ ወዲያው** በWAC 182-503-0060 ላይ ከተቀመጠው ቀነ ገደብ ሳናሳልፍ እናየዋለን።

እርስዎ ለአገልግሎቱ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን የምንፈልጋቸውን መረጃዎች እንዲሰጡን **10 ቀናት እንሰጥዎታለን።** ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለግዎት እንሰጥዎታለን። መረጃ ለእኛ ካልሰጡን ወይ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥዎት ካልጠየቁ፣ የእርስዎን የጤና ክብካቤ የመድን ሽፋን ውድቅ ልናደርግ፣ ልንዘጋ ወይም ልንለውጥ እንችላለን።

እርስዎ ለፕሮግራሙ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ወይም ማስረጃ በማግኘት ረገድ ከተቸገሩ እኛ **እናግዝዎታለን።** እኛ እርስዎን ገንዘብ የሚያስወጣ ሰነድ እንዲያቀርቡልን ከፈለግን እኛ የዚህን ማስረጃ ወጪ እንከፍላለን።

የእርስዎን የጤና ክብካቤ የመድን ሽፋን ከማስቆማችን በፊት **በአብዛኛው ሁኔታዎች ቢያንስ 10 ቀናት ቀደም ብለን እርስዎ እንዲያውቁት እናደርጋለን።**

በአብዛኛው ጊዜ በ45 ቀን ውስጥ **ውሳኔውን በፅሑፍ እናሳውቅዎታለን።** የተወሰነ አካል ጉዳተኝነት ጋር በተገናኘ የሚሰጥ የጤና ክብካቤ ሽፋን እስከ 60 ቀናት ሊወስድ ይችላል። በእርጉዝ ሴት ሕክምና ላይ በ15 ቀን ውስጥ እኛ የጽሑፍ ውሳኔ እንሰጣለን።
እኛ የእርስዎን ጉዳይ የምንመረምር ከሆነ እርስዎ ለመርማሪው ምላሽ መስጠትን **እምቢ እንዲሉ እንፈቅድልዎታለን።** መርማሪ ቤትዎ እንዲገባ መፍቀድ የለብዎትም። መርማሪውን በሌላ ጊዜ እንዲመጣ ሊጠይቁት ይችላሉ። ይህ ዓይነቱ ጥያቄ የእርስዎ የጤና ክብካቤ ሽፋን ማግኘት አለማግኘት ላይ ተጽእኖ አያደርግም።

በWAC 182-504-0125 መሠረት እርስዎ ለሌላ ፕሮግራም ብቁ መሆንዎን እኛ ብንወስንም እርስዎ **የ Washington Apple Health ሽፋን ማግኘትዎን ይቀጥሉ።**
እርስዎ ለፕሮግራሙ ብቁ ሆነው ከተገኙ በ WAC 182-503-0120 ውስጥ የተዘረዘሩትን **አገልግሎቶች እኩል እንዲያገኙ እናደርጋለን።**

## የ Washington Apple Health ጋር በተገናኘ ብቻ የእርስዎ ግዴታዎች (እርስዎ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት)

በWAC 182-504-0105 እና WAC 182-504-0110 **የሚፈለጉትን ለውጦች** ለውጡ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ **ማሳወቅ አለብዎት** ምን ለውጦች ሪፖርት ማድረግ እንደሚገባዎት ለማወቅ የፍቃድ ደብዳቤዎትን ማንበብ ይኖርብዎታል።
**እድሳት** በሚጠየቁበት ጊዜ **ያድሱት**
የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ ጥያቄ ለእኛ ለማቅረብ የሚያስፈልጉትን **የሕክምና አገልግሎት ሰጪዎች መረጃዎች ይስጡ**
እርስዎ የ **Medicare** አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ከሆኑ አገልግሎቱን ለማግኘት **ያመልክቱ**
በሚጠየቁበት ጊዜ **የጥራት ማረጋገጫ ሠራተኛ ለሚያነሳው ጥያቄ ትብብርዎን ይስጡ**
እርስዎ የ Washington Apple Health ሽፋን ለማግኘት በሚጠይቁበት ጊዜ ከሌሎች ምንጮች ገቢ ለማግኘት **ማመልከት እና ጥረት ማድረግ አለብዎት**

## እርስዎ ማወቅ ያለብዎት ነገሮች
### ለ Washington Apple Health ብቻ

**እርስዎ የ Washington Apple Health ዋስትና ለማግኘት** በመጠየቅዎ እና በማግኘትዎ ለዋሽንግተን ግዛት የሕክምና ድጋፍ መብቶች በሙሉ እና ማንኛውም የኛ ወገን የጤና ክብካቤ ክፍያ ይሰጣሉ።

**ኤጀንሲው** የእርስዎን ልጅ የክትባት ታሪክ ለልጅ ክትባት መከታተያ ሥርዓት **ሊያጋራ ይችላል።**

**እርስዎ የሚሰጡት መረጃ** እርስዎ እንደ ጤና ክብካቤ ሽፋን፣ የገንዘብ እርዳታ፣ የምግብ እርዳታ እና የልጅ ክብካቤ ድጋፍ የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ብቁ መሆን እና ወርሃዊ ጥቅማጥቅም ማግኘት መቻል ለመወሰን ለማኅበራዊ እና ጤና አገልግሎት መምሪያ ሊሰጥ ይችላል።

**በሕግ፣ የዋሽንግተን ስቴት ከእርስዎ መኖሪያ (እስቴት) ለተወሰኑ የሕክምና አገልግሎቶች የከፈለውን ገንዘብ በ Estate Recovery (RCW 41.05A.090, RCW 43.20B.080, Chapter 182-527 WAC) በኩል ሊያስመልስ ይችላል።** ንብረት ክፍያን ለማስመለስ መጠቀም እርስዎ፣ በሕይወት ያሉ የእርስዎ ባለቤት እና 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ በሕይወት ያሉ ልጆችዎ እስከሚሞቱ ድረስ ተፈፃሚ አይሆንም። ይህ በሕይወት ያለው ልጅ እርስዎ በሞቱበት ጊዜ ማየት የተሳነው/አካል ጉዳተኛ ከሆነ ይህ ከንብረት ክፍያን የማስመለስ ሂደት ተፈፃሚ አይሆንም። ተመላሽ የሚደረጉ ወጪዎች የሚያካትቱት:

- እርስዎ ይህንን አገልግሎት በወሰዱበት ጊዜ እድሜዎ 55 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ የተወሰኑ የ Washington Apple Health የረጅም ጊዜ አገልግሎት እና ድጋፍ፤
- እርስዎ አገልግሎቱን በሚያገኙበት ጊዜ በእድሜዎ ላይ ሳይመሠረት የተወሰኑ በግዛት ብቻ የሚሸፈኑ አገልግሎቶች

እርስዎ የአገልግሎቶቹን ዝርዝር WAC 182-527-2742 ሥር በተደነገገው የወጪ ማስመለስ ሂደት መሠረት ማግኘት ይችላሉ። እርስዎ በWAC 182-527-2746 ስር በተደነገገው የወጪ ማስመለስ ሂደት መሰረት ከማስመለሻው ውጪ የሆኑትን የንብረቶች ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ።

ግዛቱ እርስዎ በቋሚነት ወደ እርዳታ ተቋም ከገቡ በማንኛውም ጊዜ ከመሞትዎ በፊት በቋሚ ንብረትዎ ላይ እገዳ ሊያስተላልፍ ይችላል (WAC 182-527-2734) ግዛቱ የሚከተለው ተፈፃሚ ካልሆነ በስተቀር ክፍያውን ንብረቱን ወይም የእርስዎን ሀብት በመሸጥ ሊያስመልስ ይችላል:

- ባለቤትዎ በቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ፤
- የእርስዎ እህት እና ወንድም በቤት ውስጥ የሚኖር እና የቤቱ የጋራ ባለቤት ከሆነ እንዲሁም የተወሰኑ ግዴታዎችን የሚያሟላ ከሆነ።
- የእርስዎ ልጅ በቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ እና ማየት የተሳነው/አካል ጉዳተኛ ከሆነ፤ ወይም
- የእርስዎ ልጅ በቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ እና እድሜ ከ 21 በታች ከሆነ።

በ WAC 182-527-2734 በቅድመ ሞት ግንኙነት ስር ወጪ የማውጣት አገልግሎት ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ.

**እርስዎ ከአገልግሎት ሰጪዎች አላስፈላጊ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ከተደረገልዎት በአንድ የጤና ክብካቤ ሰጪ፣** ፋርማሲ እና/ወይም ሆስፒታል ሊገደቡ ይችላሉ።

Washington State
Health Care Authority

[English] Language assistance services, including interpreters and translation of printed materials, are available free of charge. Call 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Amharic] የቋንቋ እገዛ አገልግሎት፣ አስተርጓሚ እና የሰነዶችን ትርጉም ጨምሮ በነጻ ይገኛል። 1-877-501-2233 (TRS: 711) ይደውሉ።

[Arabic] خدمات المساعدة في اللغات، بما في ذلك المترجمين الفوريين وترجمة المواد المطبوعة، متوفرة مجاناً، اتصل على رقم 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Burmese] ဘာသာပြန်ဆိုသူများနှင့် ထုတ်ပြန်ထားသည့် စာရွက်စာတမ်းများဘာသာပြန်ခြင်းအပါအဝင် ဘာသာစကားအထောက်အကူဝန်ဆောင်မှုများကို အခမဲ့ရရှိနိုင်ပါသည်။ 1-877-501-2233 (TRS: 711) ကိုဖုန်းခေါ်ဆိုပါ။

[Cambodian] សេវាជំនួយភាសា រួមមានទាំងអ្នកបកប្រែផ្ទាល់មាត់ និង ការបកប្រែឯកសារបោះពុម្ព គឺអាចរកបានដោយឥតគិតថ្លៃ។ ហៅទូរស័ព្ទទៅលេខ 1-877-501-2233 (TRS: 711)។

[Chinese] 免费提供语言协助服务，包括口译员和印制资料翻译。请致电 1-877-501-2233 (TRS: 711)。

[Korean] 통역 서비스와 인쇄 자료 번역을 포함한 언어 지원 서비스를 무료로 이용하실 수 있습니다. 1-877-501-2233 (TRS: 711)번으로 전화하십시오.

[Laotian] ການບໍລິການດ້ານພາສາ, ລວມທັງນາຍແປພາສາ ແລະ ການແປເອກສານທີ່ພິມ, ມີໄວ້ໃຫ້ຟຣີໂດຍບໍ່ຄິດຄ່າ. ໂທຫາເລກ 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Oromo] Tajajilli gargaarsa afaanii, nama afaan hiikuu fi ragaalee maxxanfaman hiikuun, kaffaltii malee ni argattu. 1-877-501-2233 (TRS: 711) irratti bilbilaa.

[Persian] خدمات کمک زبانی، از جمله مترجم شفاهی و ترجمه اسناد و مدارک (مطالب) چاپی، بصورت رایگان ارائه خواهد شد.با شماره 1-877-501-2233 (TRS: 711) تماس بگیرید.

[Punjabi] ਭਾਸ਼ਾ ਸਹਾਇਤਾ ਸੇਵਾਵਾਂ—ਦੁਭਾਸ਼ੀਏ ਅਤੇ ਪ੍ਰਿੰਟ ਕੀਤੀ ਹੋਈ ਸਮੱਗਰੀ ਦੇ ਅੰਨੁਵਾਦ ਸਮੇਤ—ਮੁਫ਼ਤ ਉਪਲੱਬਧ ਹਨ। 1-877-501-2233 (TRS: 711) 'ਤੇ ਕਾਲ ਕਰੋ।

[Romanian] Serviciile de asistență lingvistică, inclusiv cele de interpretariat și de traducere a materialelor imprimate, sunt disponibile gratuit. Apelați 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Russian] Языковая поддержка, в том числе услуги переводчиков и перевод печатных материалов, доступна бесплатно. Позвоните по номеру 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Somali] Adeego caawimaad luuqada ah, ay ku jirto turjubaano afka ah iyo turjumid lagu sameeyo waraaqaha la daabaco, ayaa lagu helayaa lacag la'aan. Wac 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Spanish] Hay servicios de asistencia con idiomas, incluyendo intérpretes y traducción de materiales impresos, disponibles sin costo. Llame al 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Swahili] Huduma za msaada wa lugha, ikiwa ni pamoja na wakalimani na tafsiri ya nyaraka zilizochapishwa, zinapatikana bure bila ya malipo. Piga 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Tagalog] Mga serbisyong tulong sa wika, kabilang ang mga tagapagsalin at pagsasalin ng nakalimbag na mga kagamitan, ay magagamit ng walang bayad. Tumawag sa 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Tigrigna] ተርጎምትን ናይ ዝተሓተሙ ማተርያላት ትርጉምን ሓዊሱ ናይ ቋንቋ ሓገዝ ግልጋሎት፣ ብዘይ ምንም ክፍሊት ይርከቡ። ብ 1-877-501-2233 (TRS: 711) ደውሉ።

[Ukrainian] Мовна підтримка, у тому числі послуги перекладачів та переклад друкованих матеріалів, доступна безкоштовно. Зателефонуйте за номером 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Vietnamese] Các dịch vụ trợ giúp ngôn ngữ, bao gồm thông dịch viên và bản dịch tài liệu in, hiện có miễn phí. Gọi 1-877-501-2233 (TRS: 711).

HCA 65-153 (3/17) DSHS